# <u>ጻድቁ ሙሴ ጸሊም የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ መነኩሴ (330 - 405 A. D)</u>

የጥቁሮች ምድር አሕጉራችን አፍሪካ በጥንት ዘመን እንደ ዛሬ እስልምና ሳይስፋፋ ክርስትናን ቀድመው ከተቀበሉ አሕጉራት አንዷ በመሆን ብዙ የሃይማኖት ሰዎችን ያስገኘች የቅዱሳን መፍለቂያ ናት፡፡ ከእነዚህም ቅዱሳን ለአብነት ያህል የገብጻችን ከዋክብት እነ አባ እንጦንስን፣ አትናቴዎስንና ግብጻዊት ማርያምን፣ የካርቴጁን ሊቀ ቅዱስ ሲፕሪያንን እና ኢትዮጵያዊውን ጻድቅ ሙሴ ጸሊምን መጥቀስ ይቻላል፡፡
ሙሴ ጸሊም (ጥቁሩ ሙሴ) በሐዲስ ኪዳን ምናልባትም የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ መነኩሴ እንደሚሆን የሚገመት ሲሆን፣ ይህ የዋሕና ጻድቅ አባት በንስሐ ለሚመለሱ ሰዎች አምላካችን እግዚአብሔር ይቅር ባይ መሆኑን በሕይወቱ ያስተማረ ሰው ነው፡፡



ያ ዘመን ለገዳማዊ ሕይወት ጀማሪና አብነት የሆኑት ግብጻውያን የሃይማኖት አባቶች በተባሕትዎና በተህርምት ላይ ሆነው ከፈጣሪያቸው ጋር ለመገናኘት ከመኖሪያ ቤታቸው እየወጡ ወደ ጫካ የሚገቡበት፣ የግብጽ በረሃዎች ሁሉ በመናንያን የተጥለቀለቁበት ወርቃማ ዘመን ነበር፡፡ ኢትዮጵያዊው ሰው ሙሴ ጸሊም በዚህ ዘመን በግብጽ ሀገር በሰው ቤት በአገልጋይነት ተቀጥሮ ይኖር ነበር፡፡ አካለ ጠንካራ፣ ግዙፍ፣ ኃይለኛና ምንም ሰው ሊቋቋመው የማይችል ጉልበታም የነበረው ይህ ሙሴ የሚያገለግልባቸው ሰዎች የፀሐይን አምላክ ያመልኩ ስለ ነበረ እውነተኛውን አምላክ የማወቅ ፍላጎት በአምሮው ይመላለስ ነበር፡፡ እናም በፀሐይ የምትመሰል አምላክ፣ "እውነተኛ አምላክ አንተ ከሆንክ እነሆ ራስህን ግለጽልኝ" እያለ ደጋግሞ ይናገር ነበር፡፡
ሆኖም በመካከሉ በሚያገለግልበት ቤት ታማኝነትን ስላጎደለ ከቤት ወጥቶ ተባረረ፡፡ ከዚያም ወደ ጫካ ገብቶ በአባይ ወንዝ ሸለቆ እሱን መሰል 75 ኃይለኛ ወንበዴዎችን በማሰባሰብ የዛራፊዎችን ቡድን አቋቋመ፡፡ የሙሴ ኃይለኛነት የታወቀባቸው ብዙ ታሪኮች አሉ፡፡ በአንድ ወቅት ሙሴና ተባባሪዎቹ እንደ ተለመደው አንድን የታወቀ ባለ ሐብት ለመዝረፍ መንጋውን ወደ ሚጠብቅበት ሲያመሩ ግለሰቡ በውሻው ረዳትነት ንብረቱን ሳያስዘርፍ ታግሎ ራሱን አዳነ፡፡ ሙሴ በዚህ ተናዶ ግለሰቡን ለመግደል በራሱ ማለ፡፡ ከዚያም ሰይፉን በጥርሱ ይዞ የአባይን ወንዝ በዋና በማቋረጥ ከመኖሪያ ቤቱ ቢደርስ ከቤት አላገኘውም፡፡ በጎቹን አርዶ፣ ንብረቱን ዘርፎ ከተመለሰ በኋላ እንደገና በበቀለኝነት ስሜት አፈላልጎ ለመግደል ብዙ ጥረት አደረገ፡፡ ነገር ግን ግለሰቡ ፈጽሞ ርቆ በመሄድ ስለ ተሸሸገ ሊያገኘው አልቻለም፡፡




በዚያን ዘመን በመንግሥት ወታደሮች በጽኑ ይፈለግ የነበረው ይህ ኃይለኛ ሰው ሙሴ ከተከታዮቹ ጋራ ሆኖ በምዕራባዊ ግብፅ በገዳመ አስቄጥስ እየዞረ ሲዘርፍ ከዕለታት በአንድ ቀን ከአንድ ገዳም ደረሰ፡፡ ሙሴ ጸሊም ወደዚህ ገዳም የገባበትን ምክንያት አንዳንዶቹ ለዘረፋ እንደወጣ እግር ጥሎት ነው፤ ሌሎቹ መንግሥት ይፈልገው ስለ ነበረ በዚያ ሊደበቅ ፈልጎ ነው፤ ሌሎቹ ደግሞ የሚያገለግላቸው ሰዎች የሚያመልኩትን የፀሐይ አምላክ ራስህን ግለጽልኝ ብሎ በተማጸነ ጊዜ "ወደ ገዳመ አስቄጥስ ሂድ፤ በዚያ ታገኘኛ አለህ" ብሎት ስለ ነበረ ነው ይላሉ፡፡ ያም ሆነ ይህ ግን ሙሴ ወደ ገዳሙ እንደ ደረሰ የተቀበለው አባት አባ ኤስድሮስ ለጊዜው ሙሴን ተመልክቶ በታጠቀው ሰይፍና በቁመናው ግዙፍነት የተደናገጠ ቢመስልም ሙሴ ግን በቃሉም ሆነ በአስተያየቱ ያሳየው ገራምነት ያልተለመደ ነበር፡፡ አባ ኤስድሮስ ሙሴን ተከብሎ የአባ እንጦንስ ተከታይ ለነበረው ለታላቁ አባት ለአባ መቃርስ አስረከበው፡፡ ከአባ መቃርስ ጋር እንደተገናኘ ሙሴ ወዲያውኑ በቅጽበት ተለወጠና በዚያው ገዳም ከመናንያኑ ጋራ ለመኖር ጥገኝነት እንዲሰጡት ለመነ፡፡ ከዚህ በኋላ ወደ ቀደመ የጥፋት ተግባሩ አልተመለሰም፡፡ በዚያው ባለበት የምድረ በዳ ገነት በተባለው በገዳመ አስቄጥስ የብሕትውናን ሕይወት መኖር ጀመረ፡፡




አሁን ሙሴ ልቡ ፈጽሞ ተረትቶ ወደ እግዚአብሔር ተመልሷል። እግዚአብሔር የሰጠው ኃይለኛነቱ ግን አብሮት አለ፤ ቢሆንም ይህን ኃይሉን ለበጎ ነገር ብቻ ይጠቀምበታል። በአንድ አጋጣሚ እንዲህ ሆነ። ገዳማውያኑ በጸሎት ተወስነው ባሉበት ሰዓት በድንገት የበረሃ ወንበዴዎች መጥተው ገዳሙን መዝረፍ ጀመሩ። ጻድቁ ሙሴ ግን በልቡ ወደ እግዚአብሔር ቢመለስም የገዳማውያኑ ንብረት ሲዘረፍ እያየ ዝም ማለት አልፈቀደም። በጥፋት ተግባር ላይ የተሰማሩትን ወንበዴዎች ሊያስተምራቸው ፈለገና ጉልበታም ስለ ነበር ሁሉንም እየጎተተ ሰብስቦ በቁጥጥር ሥር አዋላቸው። እነሱም ይበቀለናል ክፉ ነገር ያደርግብናል ብለው ሲጠባበቁ ክርስቲያን በሰው ላይ ክፉ አያደርግም፤ እግዚአብሔር ይቅር ይበላችሁ፤ ወደ ፈለጋችሁት መሄድ ትችላላችሁ ብሎ አሰናበታቸው። እነሱም በዚህ ጻድቅ ርኅራኄና ከእግዚአብሔር በተሰጠው ጸጋና ሞገስ ተማርከው በዚያው ገዳም ከባሕታውያኑ ጋር ተቀላቅለው ቀርተዋል።

ጻድቁ ሙሴ ለመንፈሳዊ ነገር ቀናተኛ ከመሆኑ የተነሳ ፈጥኖ ከፍጹምነት ማዕርግ መድረስ ባለ መቻሉ ያዝን ነበር። የገዳሙ አባት አባ ኤስድሮስ ግን መንፈሳዊ ዕድገት ደረጃ በደረጃ የሚሰጥ እንደሆነ እየመከረ ያጽናናው ነበር። በረከትን ለማግኘት ካለው ጽኑ ፍላጎት የተነሳ በገዳሙ ውስጥ በትጋት ያገለግል ነበር። ገዳማውያኑም በአገልግሎቱ ይደሰቱ ነበር። ጉልበታም ስለነበረ ባሕታውያኑ ውሃ የሚይዙባት ትንሽ ቅል ስትጎድልባቸው ሳያዩ በየበዓታቸው እየሄደ ተደብቆ ይሞላላቸው ነበር።

ሆኖም ይህን በጎ አገልግሎቱንና መንፈሳዊ ቀናተኛነቱን ሰይጣን ስላልወደደለት በብዙ የጾር ዓይነቶች ክፉኛ ይፈታተነው ነበር። የበጎ ነገር ሁሉ ጠላት የሆነው ሰይጣን ጻድቁ ሙሴን በልዩ ልዩ መንፈድ ፈትኖ ሊያሸንፈው ባለመቻሉ በአንድ ወቅት በቀጥታ በሰው ተመስሎ በመቅረብ እግሩን በድንጋይ ቀጥቅጦ ለረዥም ጊዜ ታሞ አልጋ ላይ እንዲውል አድርጎታል። ሙሴ ግን ፈተናው የሰይጣን መሆኑን ስለሚያውቅ ሰውነቱ የተቃጠለ ግንድ እስከ ሚመስል ድረስ በተጋድሎው የበለጠ ይተጋ ነበር። እግዚአብሔርም ጽናቱን አይቶ ከደዌው ፈውሶታል።

ጻድቁ ሙሴ ልቡ ቅን ውስጡ ንጹሕ ስለ ነበር እንደተመኘው በመንፈሳዊ ጸጋ አድጎ ከደጋጎች ተራ ለመሰለፍ ጊዜ አልወሰደበትም። ከዕለታት በአንድ ቀን በታላቁ አባት በአባ መቃርዮስ ፊት ቀርቦ እንባውን እያፈሰሰ ያለፈ ኃጢአቱን መናዘዝ ጀመረ። በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር መላክ በፊቱ ቆሞ በደሉን በጽላት ላይ ጽፎ ያሳየው ነበር። ሙሴ ምርር ብሎ እያለቀሰ ኃጢአቱን በተናዘዘ ቁጥር መልአኩ በደሉን ከሰሌዳው ላይ እየጠረገ ያጸዳ ነበር። በመጨረሻም ሙሴ ሁሉንም የሚያስታውሰውን ያህል ተናዞ ሲጨርስ መልአኩ ሰሌዳውን ንጹሕ አድርጎ አጽድቶ ከፊቱ ተሰውሯል።




ጻድቁ ሙሴ በገዳም ሲኖር አባቶችን ለመርዳት ካልሆነ በቀር ከግል ዋሻው አይወጣም ነበር። በዚህ ሁኔታ በገዳማዊ ሕይወቱና በአገልግሎቱ የተመሰገነ አባት ሆኖ ከቆየ በኋላ በአባ መቃርዮስ እጅ ምንኩስናን ተቀበለ። በ75 ዓመቱ ከግብፅ ፓትርያርክ ከአባ ቴዎፍሎስ 23ኛ ቅስናን ለመቀበል በተዘጋጀበት ወቅት ፓትርያርኩ ደግነቱን ለመፈተን፣ “ይህ ጥቁር ኢትዮጵያዊ ማን ነው? እዚህ ምን እያደረገ ነው?” ብለው በመናገራቸው ለእኔ ቅስና አይገባኝም ብሎ በቀስታ ከቤተ ክርስቲያን ወጥቶ ሄደ። በኋላ ግን ፓትርያርኩ ካለበት ጠርተው የቅስናን ማዕርግ ከሰጡት በኋላ “አንተ ጥቁር አይደለህም፤ ልብህ ነጭ ነው” ብለውታል። ከዚያ በኋላ ገደም ከመግባቱ በፊት በዱር በገደል ይዞር በነበረበት ጊዜ ባሰባሰባቸው ወንበዴዎች ቁጥር 75 መነኮሳት ያሉበት ራሱን የቻለ ገዳም መሠረተ። ገዳሙ አድጎ የአባላቱ ቁጥር 500 ሲደርስ በገዳማውያኑ ጥያቄ የገዳሙ አበምኔት እንዲሆን ተመረጠ።

በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ጥበበኛ፣ ትሁትና በሰው ላይ መፍረድ የማይወድ ደግ ባሕታዊ የነበረው ይህ ኢትዮጵያዊው መነኩሴ ከብዙ ተጋድሎ በኋላ ከብቃት ማዕርግ ደርሶ ልዩ ልዩ ተአምራትን ያደርግ የነበረ ሲሆን፣ የተናገራቸውም ምርጥ ምርጥ ቃላት በምዕራባውያን ክርስቲያኖች ዘንድ እስከ አሁንም ድረስ ይጠቀሳሉ። ከዕለታት በአንድ ቀን ያገለግል በነበረበት ጋዳም በደል ፈጽሞ በተገኘ በአንድ መነኩሴ ላይ በገዳሙ ሥርዓት መሠረት ፍርድ ለማስተላለፍ የሰዎች ሐሳብ አስፈላጊ ስለ ነበር በገዳሙ አበምኔት በኩል ተጠርቶ የመሰለውን ፍርድ እንዲያስቀምጥ ታዘዘ። እሱ ግን ሲመጣ በቀዳዳ ጆንያ አሸዋ ሞልቶ በትክሻው ላይ ተሸክሞ ነበር። ለምን እንዲህ አደረግህ አባታችን ቢሉት "የእኔ ኃጢአት ከኋላየ ያለማቋረጥ ይዘረከረካል፤ ለእኔ አይታየኝም፤ ነገር ግን ደግሞ ራሴን ጻድቅ አድርጌ በሰው ላይ ልፈርድ ተዘጋጅቻለሁ" አላቸው። በዚህ ጊዜ ተደናግጠው ያን ግለሰብ ነጻ ለቀው ስለ ራሳቸው እያለቀሱ ወደ እየቤታቸው ገብተዋል።



ጻድቁ ሙሴ የሕይወቱ ፍጻሜ በሰማዕትነት እንደሆነ ከእግዚአብሔር ስለ ተነገረው ያችን ቀን በናፍቆት ይጠባበቅ ነበር። በ405 ዓ. ም. አንድ ቀን ከጥቂት መኖኮሳት ጋራ ሆኖ ወደ ታላቁ አባት ወደ አባ መቃርዮስ ሊጠይቀው ሄደ። እዚያ እንደ ደረሰ ይህ ምሥጢር ለአባ መቃርዮስም ተገልጦለት ስለነበር፣ "ከመካከላችሁ አንዱ የሰማዕትነት አክሊል ጭኖ አያለሁ" አላቸው። ሙሴም በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 26 ቀጥር 25 "ሰይፍን የመዘዙ ሁሉ በሰይፍ ይጠፋሉ" የሚል ቃል የተጻፈ መሆኑን በመጥቀስ "ምን አልባት እኔ እሆናለሁ" ሲል መለሰ። ይህን በተናገረ በጥቂት ቀናት ውስጥ ሃይማኖት የለሽ አረመኔዎች በዚያ በረሃ ውስጥ ክርስቲያኖች ገዳም መሥርተው መኖራቸውን ስምተው እነርሱን ሊያጠፉ ታጥቀው መጡ። ሙሴ ግን ይህ እንደ ሚሆን አስቀድሞ ለገዳማውያኑ ተናግሮ ቀኑ ሲደርስ ወጥተው እንዲጠፉ መከራቸው። አባት ሆይ አንተሳ ብለው ቢጠይቁት እኔማ ይህችን ቀን በናፍቆት ነው ስጠባበቅ የቆየሁት አላቸው። ያለው አልቀረም አረመኔዎች ወደ ገዳሙ ገብተው ሙሴን ከሌሎች ሰባት ባሕታውያን ጋር አንገቱን በሰይፍ ቀሉት። በዚህ ሰዓት አንድ አባት ተደብቆ የሚሆነውን ነገር ሁሉ ሲመለከት የእግዚአብሔር መልአክ በእጁ አክሊል ይዞ የሙሴ አንገት በሰይፍ እስከሚቀላ ድረስ ይጠባበቀው ነበር። ይህን ካየ በኋላ እሱም ከተሸሸገበት ወጥቶ እንደ ወንድሞቹ በሰይፍ ተከልሎ የሰማዕትነትን ክብር አግኝቷል።

የጻድቁ ሙሴ የዕረፍት ቀን በመላው የኦርቶዶክስና የካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ከጥንታዊያን ጻድቃን እንደ አንዱ ሆኖ በከፍተኛ ደረጃ ይታሰባል። በትውልድ ሀገሩ በኢትዮጵያ ግን ጻድቅ መሆኑን አምኖ ከመቀበል ያለፈ ብዙም የሚታወቅ አይደለም። ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የጻድቁን የዕረፍት ቀን ከማሰብ አልፎ በስሙ ገዳማትን መሥርተዋል። ለምሳሌ በ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በሶርያ አገር Mar Mousa al-Habashi የተባለ ገዳም በጻድቁ በሙሴ ስም ተመሥርቷል። ይህ ገዳም በአሁኑ ዘመን የቱሪስት መስህብ ከሆኑ የእምነት ማዕከላት አንዱ ነው። ገዳሙ በውስጡ ጥንታውያን የሆኑ አስደናቂ ስዕሎች ያሉበት ሲሆን የተመሠረተውም በተራራ ጫፍ ላይ ነው።

የዚህ ጻድቅ ጸሎቱ፣ ጸጋውና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይሁን፤ ለዘለዓለሙ አሜን።

ቀሲስ ዘመነ አቡሐይ

ካሊፎርንያ